# በፌዴራል ጤና ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
# ዜና ኢ.ሕ.ጤ.ኢ.

ሚያዚያ 2013 ቅጽ 5 ቁጥር 1

በኢ.ሕ.ጤ.ኢ. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ

## አዲስ የምግብ ደህንነት ላቦራቶሪ ተከፈተ



የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ውስጥ የሚገኘዉ የምግብ ሳይንስ እና ኒዉትሪሽን ዳይሬክቶሬት በዘመናዊ መልኩ የተሰራ የምግብ ደህንነትና የምግብ ማይክሮ ባዮሎጂ የምርምር ኬዝቲም ላብራቶሪ የኢንስቲትዩቱ ዋና እና ምክትል ዳይሬክተሮች በተገኙበት አስመረቀ ። ይህ ላብራቶሪ በኢትዮጵያ ብቸኛ የሆነዉ ላብራቶሪ ሲሆን ረጅም አመታት ሲሰራበት የቆየ ህንፃ በማርጀቱና ጠባብ በመሆኑ ለስራ አመቺ እና ከወቅቱ ና ከጊዜዉ ጋር የሚሄድ ባለመሆኑ ላብራቶሪዉ አዲስና ዘመናዊ ላብራቶሪ መገንባት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በዘመናዊ መልክ ሊሰራ እንደተቻለ፣ ላብራቶሪዉ አገልግሎት የዉሃ ወለድ እና የዉሃ ወለድ ወረርሽኝ ላይ እንደሚሰራ የችግሩ መነሻ ምክንያት ላይ ምርመራ እና ምግብ ና ዉሀ ጥራት ና ደህንነት ምርመራ እንደሚያካሂድ በምረቃ ፕሮግራሙ ተገልጽዋል፡ ፡ በፕሮግራሙ ላይ የተገኙት የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር ኤባ አባተ ላብራቶሪዉን ለመገንባት ብዙ ጊዜ እንደፈጀ እና ወደ 7 ሚሊዮን ብር እንደፈጀ ገልፀዋል።

## የጨቅላ ህጻናትን ሞት ለመቀነስ ከፍተኛ ስራ መሰራት እንዳለበት ተገለጸ



በኢትዬጵያ የጨቅላ ህፃናት ሞት መጠን ከ1ሺህ በህይወት ከሚወለዱት 33ቱ ለህልፈት ይዳረጋሉ ይህም በፈረንጆቹ በ2016 ከነበረው አህዝ (29 ሞት/1ሺህ ህጻናት) ጭማሪ አሳይቷል።
በመሆኑም በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ምርምር ትግበራ ዳይሬክቶሬት (Knowledge Translation Directorate) የጨቅላ ህጻናትን ሞት ለመቀነስ ያስችል ዘንድ ከ 28-29/08/13 ዓ.ም በቀረበዉ የፖሊሲ ብሪፍ (evidence brief for policy) በቢሾፍቱ ከተማ ዉይይት ተካሂዷል። በመድረኩ ላይም የፓርላማ አባላትና፣ ጤና ሚኒስቴርን ጨምሮ ሌሎች ባለድረሻ አካላት በተገኙበት ዉይይት (Policy Dialogue) ተካሂዷል።
በውይይቱም ጨቅላ ህፃናት መታፈን (Asphyxia)፣ ኢንፌክሽን እና ጊዜያቸው ሳይደርስ የሚወለዱ ህፃናት፣ ለጨቅላ ህፃናት ሞት ዋነኛ ምክንያት ናቸው ተብለው ተለይተዋል። በተጨማሪም የቅድመ ወሊድ ክትትል አለማድረግ ፣ በጤና ተቋማት አለመውለድ ቢወለዱም በቂ እና ጥራት ያለው አገልግሎት አለማግኘት፣ ሌሎች ምክንያቶች ናቸው ተብለው ተነስተዋል።
በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የምርምር ትግበራ ዳይሬክቶሬት ተ/ዳይሬክተር የሆኑት ወ/ት ፊርማዬ እንደገለጹት የምክክሩ ዋነኛ ዓላማ የጨቅላ ህጻናትን ሞት ለመቀነስ የሚደረገውን ሀገር አቀፍ እንቅስቃሴ በመረጃ መደገፍና

. . .ወደ ገጽ 3 ዞሯል

# የጤና ሚኒሰቴር/የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከአሜሪካ በሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከል የኮቪድ-19 ምላሽ ላይ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ



የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከጤና ሚኒስቴር ፣ ከክልል ጤና ቢሮዎች እና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በሃገራችን የሕብረተሰብ ጤና ስጋቶች ላይ የቁጥጥር እና ምላሽ ስራዎችን ፣የላቦራቶሪ አቅም ግንባታ እና የጤና ምርምር ተግባራቶች ላይ በመስራት ላይ ይገኛል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአገራችን ብሎም በአለማችን ቁጥር አንድ የአለምአቀፍ የህብረተሰብ ጤና ስጋት የሆነዉም ወደ አገራችን ከመግባቱ በፊት የህብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበሪያ ማእከል አቋቁሞ የቅድመዝግጅት ተግባራቶች ወደ አገራችን ከገባ በ ኋ ላ ከባለድርሻ አካላት እና አጋር አካላቶች ጋር በመሆን አስፈላጊዉን ምላሽ እየሰጠ ይገኛል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ ከአጋር አካላት ጋር በመሆን በተለዩ ድጋፎች ማለትም በሰዉ ሃይል፣በግብአት እና በፋ ይ ናንስ የምላሽ አቅምን ከመገንባት አንታር የአጋር አካላት ሚና ወሳን መሆኑ ይታወቃል፡ ፡ከነዚህም አጋር አካላት የአሜሪካ የበሽታ መከላከል እና መቆጣጠር መእከከል በአገራችን የቴና አገልግሎት ከማገዝ አኳያ አንዱ አጋራችን መሆኑ ይታወቃል። ከዚህም ጋር ተያይዞ በአገራችን ቁጥር አንድ የህብረተሰብ ጤና አደጋ የሆነዉን የኮቪድ 19 ምላሽ ስራዎችን ለማጠናከር የጤና ስርአታችንን መገንባት ላይ ማለትም የበሽታዎች ቅኝት እና አሰሳ ማጠናከር፣ የላቦራቶሪ አቅም ግንባታን ከማስፋት እና ማጠናከር፣ የህብረተሰብ ጤና አደጋ ማስተባበሪያ ከማስፋት እና ማጎልበት፣የጤና ባለሙያዎችን አቅም ግንባታ ከማጠናከር አኳያ ተኩረት ያደረገ የጤና አገልግሎቶችን ለህብረተቡ ተሰራሽ ከማድረግ ከኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት አሁን እየሰታቸን የሚገኙ የምላሽ ስራዎችን ከማጠናከር ባዘጋጀዉ የድጋፍ እቅድ ከ የአሜሪካ የበሽታ መከላከል እና መቆጣጠር መእከል ጋር የ20 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በጀት የጋራ ስምምነት አድርጎ ወደ ትግበራ ለመግባት አስፈላጊዉን ቅድመ ዝግጅት አድርጓል። ይህ ትግበራ የኮቪድ-19 ስራዎችን እና ሌሎችን የህበረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ከማሳለት፣እና ከማጠናቀር ለአገራችን ጠና ስርአት አፈታጠም ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኮሮና ቫይረስ ምላሽ ላይ ያተኮረ ፕሮጀክት አፈጻጸምን ይመራል፣ ስትራቴጂዊ የስራ አፈጻጸምን ማለትም የድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ፣ ቅኝት፣ የሰው ሃይል ማደራጀት፣ የመረጃ ስርዓት እና የላቦራቶሪ ድጋፍ ለኮቪድ 19 ምላሽ ያካሂዳል። የአሜሪካ በሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከል በብሔራዊ እና በክልል ደረጃ የኮቪድ 19 ምላሽ ስራዎች የደገፈ ሲሆን የክትባት ስረጭትም እንዲሳለጥ የበኩሉን አድረጓል፡ ፡

ከኮቪድ 19 ወረርሽን የተማርነው እንዴት የአንድ ወረርሽኝ ስጋት ምን ያክል ባልተጠበቀ ሁኔታ እና ፍጥነት እንደሚሰራጭ ነው። የኮቪድ 19 ወረርሽኝ መሰረታዊ የሕብረተሰብ ጤና የቅኝት ስራዎች እና ምላሽ አሰጣጥን፣ የሰው ሀይል ለማትን፣ እና ተዛማጅ የላቦራቶሪ እና መረጃ ስርዓትን ለማጠናከር እንደመልካም እድል ይታያል። ፕሮጀክቱ በኢትዮጵያ የበሽታ ቅኝትን፣ የላቦራቶሪ ስርዓትን፣ ኢንፍሉዌንዛ መሰል በሽታን ለመከላከል፣ ከባድ አጣዳፊ የመተንፈሻ አካላት በሽታን ለመከላከል፣ የአስቸኳይ ጊዜ ስራዎች ማዕከላት መረብን፣ የመስክ ኤፒዲሚዮሎጂ የሥልጠና ፕሮግራምን፣ ተከታታይ ክትባቶችን፣ የኮቪድ 19 ክትባት ስርጭትን እና የበሽታ መከላከል እና መቆጣጠር ሂደቶችን

. . .ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## . . . የጤና ሚኒስቴር

ከገጽ 2 የዞረ

ያጠናክራል ይደግፋል። ያለውን የሕብረተሰብ ጤና መሠረተ ልማት ከኢትዮጵያ የዝግጁነት እና ምላሽ ዕቅድ መሰረት የኮቪድ 19 ን ባለው የጤና ስርዓት ውስጥ መካተትን እና ባልተማከለ መልክ ምላሽ መስጠትን ፕሮጀክቱ አጥብቆ የሚሰራበት ጉዳይ ነው። ባለፈው ዓመት የአሜሪካ በሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከል የኢትዮጵያን ለኮቪድ 19 እንድትዘጋጅ እና ምላሽ አሰጣጥ ላይ የተለያዩ ድጋፎች ሲያደርግ ቆይቷል፣ ከነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- ዝግጁነት እና ምላሽ አሰጣጥ ላይ ስልጠናዎች መስጠት
- የድንገተኛ ስራዎች ላይ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት፣ የላቦራቶሪ ስራዎች ፣ በሽታ መከላከል እና መቆጣጠር ፣ ወደ ሀገር መግቢያ በሮች ላይ የሙቀት ልየታ ስራ፣ የአደጋ ጊዜ ተግባቦት እና የማሕበረሰብ ተሳትፎ እና የበሽታ ቅኝት ላይ ድጋፎችን አድርጓል።
- ተከታታይ ክትባቶች አገልግሎት እና ስረዓት ማጠናከር እና
- የመስክ ኤፒዲሞሎጂ ስልጠና መስጠት ናቸው።





ይህ ድጋፍ የአሜሪካውን የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከልን ሌሎችን የኢንስቲትጡቱን ተልእኮ ከማስፈጸም ሲያደርግ የነበረውን የረጅም ጊዜ ጥረት እና እርዳታ የሚያዳብር ነው። የማዕከሉ የኢትዮጵያ የጤና ደህንነትን ለማሻሻል የሚያደርገው ድጋፍ ሀገሪቱን ለሚጠሩ የጤና አደጋዎች ኮሮና ቫይረስን ጨምሮ በብቃት ፈጣን ምላሽ መስጠት ከፍተና ሚና ይጫወታል።

## . . . የጨቅላ ሕጻናትን ሞት

ከገጽ 1 የዞረ

ብሄራዊ የጨቅላ ህጻናትና ልጆች ስትራቴጂ (national newborn and child survival strategy) ግብአት እንዲሆን ማድረግ ነዉ። በተጨማሪም ባለፉት 10 አመታት የእናቶች ሞትን መቀነስ ቢቻልም፣ የጨቅላ ህጻናትን ሞት መቀነስ ባለመቻሉ ከፍተኛ ትኩረት የሚሻበት ደረጃ ላይ መድረሱን ጠቁመው፣ ለዚህም የተለያዩ የመፍትሄ ሀሳቦች የተለዩ ሲሆን ማህበረሰብ አቀፍ የጤና አገልግሎትን ማጠናከርና ተያያዥነት ባለው መልኩ ከቅድመ እርግዝና ጀምሮ የእናቶችና የጨቅላ ህጻናትን የጤና አገልግሎት ማጠናከርና በየደረጃው ለሚሰጠው



አገልግሎት የጥራት ደረጃ ማስቀመጥ ፣ ከግብአት አቅርቦት እና መሰረተ ልማት ጋር የተገናኙ ችግሮችን መፍታት ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ጠቀሰዋል።

# የብሔራዊ የወባ ቅኝት ጠቋሚ ጣቢያዎች ስራ መጀመር ላይ አውደ ጥናት ተካሄደ



የኢንስቲትዩቱ የባክቲዮሮሎጂ፣ ፓራሲቶሎጂ እና የእንስሳት- ነክ በሽታዎች ምርምር ዳይሬክቶሬት ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ በተመረጡ 25 ጤና ጣቢያዎች ማለትም የወባ ቅኝት ጠቋሚ ላይ የተቀናጀ የወባን ቅኝት ስራን ተግባራዊ ያደረገበትን አስመልክቶ የምርምር ስርፀት አውደ ጥናት ከሚያዝያ 12013 ዓ.ም. ጀምሮ አካሄደ። ከጤና ሚኒስቴር ብሄራዊ የወባ ማስወገድ መሪ ሚኒስቴሩን ወክለው የተገኙ ሲሆን ከየክልሉ የጤና ጣቢያዎቹ ተወካዮችና ባለሞያዎችም እየተሳተፉ ይገኛል። በዐውደ ጥናቱ የቅኝት ስራው ስኬቶችና ተግዳሮቶች እንዲሁም የስራውን ቀጣይነትና ጥራት በማስጠበቅ ለወባ ማስወገድ ያለውን ፋይዳ መሰረት ያደረገ ውይይት እንደሚካሄድ መርዐ-ግብሩ ያመላክታል። የተጠኑ ጥናቶች ላይ እና የአቅም ግንባታ ስራዎች፣ እስካሁን በተሰራው ስራዎች የተገኙ ውጤቶች እና ተግዳሮቶች፣ ጥቅም ላይ የዋሉ ቴክኖሎጂዎች እናም ስራው ቀጣይነት እንዲኖረው ምን መደረግ እንዳለበት ከክልል የቅኝት ጣቢዎች እና ከጤና ሚኒስቴር የተወከሉ ባሉሙያዎች በተገኙበት ውይይት እየተደረገ ይገኛል። ዶ/ር ገረመው ጣሰው የዳይሬክቶሬቱ ዳይሬክተር በመክፈቻ ንግግራቸው በኢትዮጵያ የወባ በሽታ ካሉት የጤና ስጋቶች አንዱ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የምጣኔ ሀብት ተግዳሮት ጭምር መሆንን ገልፀው የሀገሪቱን ሶስት አራተኛ በሚሸፍኑ ቦታዎች መተላለፍ የሚችልና በነዚህ ቦታዎች ላይ ሰፍረው ያሉ የማህበረሰብ በግምት ከግማሽ በላይ ዜጎች ለበሽታው ተጋላጭ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። ባለፉት ዓመታት ከፍተኛ የወባ መቀነስ መመዝገብ በተመረጡ ቦታዎች የማስወገድ ስራ ማሳያ ተደርገው የሚወሰድና በሚቀጥሉ ዓመታት የወባ ማስወገድ ሥራው በሁሉም ወባማ ቦታዎች ተግባራዊ እንደሚሆን ተማላክተዋል። ሆኖም ግን ከአንድ ዓመት በፊት የተደራጀ የጤና ሚኒስቴር ዘገባ እንደሚያመለክተው ከአምስት ሚሊዮን በላይ ሰዎች የወባ ምርመራ ተካሂዶላቸው ወደ አንድሚሊዮን የሚጠጋ ሰዎች በሽታው ተገኝቶባቸው ተገቢውን ሕክም አገልገሎት ሲያገኙ ከ15 ሺህ በላይ ለወባ ተኝተው የታከሙ ሲሆን በሽታው የተባባሰ ደረጃ ላይ የደረሱና መቋቋም ያልቻሉ ከሁለት መቶ በላይ ሰዎች ደግሞ ህይወታቸው ማለፉን መረጃው ያሳያል ። የወባ ቅኝት ጠቋሚ ጣቢያዎች አስፈላገነትንና ዓላማን አስመልክቶ የፕሮጀክቱ ዋና አስተባባሪ ሲገልፁ የቅኝት ስራው የሚካሄደው የተለያዩ መልክዐ-ምድራዊ አቀማመጥ ካለቸውና የወባ ሥርጭት ያላቸው እንዲሁም የወረርሽ ታሪክና ስጋት ካለቸው 25 ጤና ጣቢያዎች ተመርጠው የወባ ተህዋስና ትንኝ ብግርነት የበሽታው ጫና የደረሰበትን ተዓማንነት ባለው መልኩ መረጃ የማመንጨትና ለወባ ማስወገድ ስራ የሚረዱ ሀገር አቀፍ ውሳኔ ለመስጠት የሚያበቃ መሰረተ-ሰፊ መረጃ ለጤና ሚኒስቴርና አጋር ድርጅቶች ለማቅረብ የሚውልይሆንል፡ ፡ በተጨማሪም የአየር ንብረት መለዋወጥን መረጃ በመከታተል ጣቢያዎቹ የወባ ወረርሽኝ ስጋት ቀድመው በመለየት የቅድመ- ዝግጅት እቅድ ማዘጋጀት ማስቻል ነው። የተጠቀሱትን መረጃዎች ለማመንጨት የሚያስችል የባለሞያ አቅምና ለጣቢያዎቹ የተለያዩ የግብዓት ማሟላት ስራዎች በስፋት ተከናውኗል፡ ፡ ከነዚህም የመረጃልውውጥን አሁናዊነት ለማረጋገጥና በቴክኖሎጂ ለመታገዝ የሞባይል መተግበሪያ ስራ ላይ ማዋል የተቻለ ሲሆን የመረጃ ጥራትን ለማረጋጥም ስልጠና ብቻ ሳይሆን በተፈለገ ጊዜ ድጋፍ የሚሰጡ የኢንስቲትዩቱ ባለሞያ በቂ ድጋፍ እደረገ ይገኛል። በስተመጨረሻም አጠቃላይ ውይይት የተካሄደ ሲሆን ከላቦራቶሪ ግብአቶችና የባለሞያ የአቅም ግንባታ ስልጠና እንዲሁም የጥራት ቁጥጥር ስልትማስረፅ ትኩረት እንደሚገባው ከተሳታፊዎችና አስተባባሪዎች ግልፅና ሰፊ ውይይት ተካሂዶ ለወደፊት የትኩረት አቅጣጫዎች ተለይተው የጋራ መግባባት ላይ ተደርሷል። የቅኝት ስራ ወባን ከማስወገድ አንፃር ያለለው ሚና በጠቋሚ ጣቢያዎች እንደማሳያ ከፍተኛ ሚና የሚጠበቅ መሆኑንና ጤና ሚኒሰተርም አስፈላጊውን የሀብት ማሰባሰብና አቅርቦት ብቻ ሳይሆን የቴክኒካዊ ድጋፍ በመስጠት ክትትል እንደሚደረግ አቶ ሙብራህቶም ሀይሌ የጤና ጥበቃ የወባ ማስወገድ ፕሮግራም ሀላፊ በመዝጊያ ፕሮግራሙ ላይ ትኩረት የሚሻ መሆኑን ገልፀዋል፡